ለማኅበረሰብ አብረው የሚታገሉበት በወዝ—አደሮችና በገበሬዎች ላይ የተመሠረተ፣ ከሰፊው ሕዝብ ክፍሎች ሁሉ የተውጣጣ ዲሞክራሲያዊና ሕዝባዊ የሆነ መንግሥት ለማቋቋም አብረው የሚታገሉበት የፖለቲካ ግንባር ያስፈልጋቸዋል::

ይህም ማለት የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግንባር መቋቋም አጣዳፊ የጊዜው ጥያቄ ነው ማለት ነው:: የፖለቲካ ፓርቲዎችን የማቋቋም ኃላፊነት የሚወድቀው የሰፊው ሕዝብ ክፍል የሆኑ ልዩ ልዩ ወደቦች ግንባር ቀደሞቶች በተለይም በነቃት ወዝ—አደሮችና በተራማጅ ምሁራን ላይ ነው:: እርግጥ የሰፊው ሕዝብ የፖለቲካ መብት መገፈፍና አምባገነናዊና ፋሽስታዊ የሆነ የምርጥ ወታደሮች ቡድን አገዛዝ ሕዝቡ በፖለቲካ ፓርቲዎች ቀርቶ በሙያ ማኅበሮች እንኳን እንዳይደራጁ ብዙ እንቅፋቶችን ፈጥሯል::

የወታደሩ አምባገነን መንግሥት ካልተገደደ በስተቀር የፈለገውን ያህል ቢከፋ ቢሰጥም የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊያን መብቶች የማያስከብር መሆኑን ተገንዝበን መደራጀትና ማደራጀት መቻል ይኖርብናል::

ሬቮሉሽን በአንዱ ደርግ ወይንም ኮሚቴ ተደርጉ እንደማያውቅ ሁሉ ነጻነትና መብትም ከገዢዎች በስጦታ መልክ ለሕዝብ ቀርቦ አያውቅም:: የነጻነት ጉዳና ተደራጅቶ መታገል ነው::

- የገበሬዎች ማኅበራት ከመንግሥት ተጽዕኖና ቁጥጥር ነጻ ይሁኑ፣
- የወዝ—አደርና የገበሬ አንድነት ይጠንክር፣
- የሰፊው ሕዝብ መሠረታዊያን የዲሞክራሲ መብቶች ይጠበቁ፣
- የታሠሩ ተራማጅ ዘማቾችና የገበሬ ማኅበራት መሪዎች እንዲሁም የወዝ—አደር መሪዎች በአስቸኳይ ይፈቱ::

ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል!!!